## እነ ምላስ መንታ!



ያሉት ተሚጠፉ የወለዱት ይጥፉ፣
ተቅድመ አያቶች ጋር ቅብር ብሏል ለካ፡፡

ጠጉራቸውን ቀብተው መልክ እየቀሩ፣
አምና የተፉትን ዘንድሮ እየዋጡ፣
እነ መንታ ምላስ አገር ሕዝብ ፈቱ፡፡

የአራዊት ደንብ እንጅ ሕግ የለ እንዳላሉ፣
ሕዝብ ለማናከስ የጫረውን እብዱ፣
ዛሬ በፓስተር አፍ እየተናገሩ፣
መጣፍ ቅዱሳቸው አርገውት አረፉ፡፡

እንደ እስስት ቆዳ መልክ እየለወጡ፣
ፕሮፌሰር ዶክተር ምሁር ነን እያሉ፣
የሕዝብ ልብ ጠብሰው አንጀት አሳረሩ፡፡

እንደ ዶሮ እንቁላል ቃል እየሰበሩ፣
ቅድም የማሉትን አሁን እየካዱ፣
የቅጥፈት ትክትክ ውሸት እየሳሉ፣
በእውነት እጀ ጠባብ አፍንጫ ጠረጉ፡፡

አምና ንስር መስሎ ዛሬ ሲሆን ጀፌው፣
ጣረሞትን እንጅ ምኑን አለማየሁ፡፡

እድሜ ታልመዘነው ዲግሪውም ታለካው፣
ትልቅ ሰው መስፈሪያ ምን ቁና ሊሆን ነው?

ሥጋቸው ሲደክም ሲዝል ጉልበታቸው፣
ውድ ሽማግሌ መሆን ሲገባቸው፣
ረክሰው አረፉት አቢይ ካድሬ ሆነው፡፡

ዘመን እየገፋ እግር ጉድጓድ ሲገባ፣
ኑዛዜ ንስሃ በመቀበል ፋንታ፣
ጆሮ ጠቢ አፍቅረው ከነፉ እንደ ዝና!

ጠዋት የሰው ምሁር እስስት ወደ ማታ፣
እንዳማሩ አይሞቱ እነ ምላስ መንታ!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ግንቦት ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.